## የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ቤትና የመገልገያ ዕቃዎች ድልድልና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር …. / 2016

ኢንስቲትዩቱ የሠራተኞችን ዕውቀትና ክህሎት በተሻለ ሁኔታ ለመጠቀም ከሚገለገልባቸው ስልቶች መካከል ለምርምር ሥራ ምቹ የሥራ አካባቢን ከመፍጠር ጋር ተያይዞ ሠራተኞች ምርምሩ በሚካሄድበት አካባቢ በቅርበት በመኖር የምርምሩን ሥራ በተረጋጋ ሁኔታ እንዲያከናውኑ የመኖሪያ ቤት በተገነባላቸው ማዕከላት የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም በነባሩ መመሪያ ላይ የነበሩ ክፍተቶችን ለማሻሻል፣ በአዲሱ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት ምክንያት የተፈጠሩ የሥራ መደቦችን ለማካተት እና ከወቅቱ ጋር የሚጣጣም የተሻሻለው የኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ቤትና የመገልገያ ዕቃዎች ድልድልና አጠቃቀም መመሪያ ወጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ** ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ቤትና የመገልገያ ዕቃዎች ድልድልና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር …. / 2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1 ኢንስቲትዩት፡- ማለት የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ነው፡፡

2.2 ማዕከል፡- ማለት በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ስር በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የስራ ቦታዎች ናቸው፡፡

2.3 የኢንስቲትዩቱ መኖሪያ ቤቶች፡- ማለት ኢንስቲትዩቱ ለሠራተኞች በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት ተከራይተው ወይም እንደስራው አስፈላጊነት ያለኪራይ እንዲኖሩባቸው ያሰራቸው

ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በሚደረግ ስምምነት የተከራያቸው መኖሪያ ቤቶች ናቸው፡፡

2.4 ለግል አገልግሎት የሚሰጥ መኖሪያ ቤት፡- ማለት አንድ ሠራተኛ ከቤተሰቦቹ ጋር ለመኖር የሚያስችል የቤተሰብ ቁጥርን ግምት ውስጥ በማስገባት በኢንስቲትዩቱ የተገነባ ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በሚደረግ ስምምነት የተከራየውን መኖሪያ ቤት ቤተሰቡን ይዞ እንዲኖርበት በኪራይ ወይም በሥራው አስፈላጊነት ያለ ክፍያ እንዲኖርበት የተፈቀደለት ቤት ነው፡፡

2.5 በጋራ የሚሰጥ መኖሪያ ቤት፡- ማለት እንደአስፈላጊነቱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሠራተኞች በጋራ እንዲኖሩበት የተፈቀደ ቤት ነው፡፡

2.6 የመኖሪያ ቤት ደረጃ፡- ማለት በኢንስቲትዩቱ የተሰሩ መኖሪያ ቤቶች በሚኖራቸው የመኝታ ክፍሎች ብዛትን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ባለ ሦስት መኝታ ቤት ደረጃ 1፣ ባለ ሁለት መኝታ ቤት ደረጃ 2፣ ባለ አንድ መኝታ ቤት ደረጃ 3፣ ባለ አንድ ክፍልና የጋራ ሳሎንና ኩሽና ደረጃ 4 እንዲሁም ባለ አንድ ክፍል ብቻ ደረጃ 5 ነው፡፡

2.7 የቤት መገልገያ ዕቃ፡- ማለት በማዕከሉ መኖሪያ ቤት ውስጥ እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው ሠራተኞች እንዲገለገሉባቸው የሚሰጧቸው የቤት ቁሳቁሶች ናቸው፡፡

2.8 ሠራተኛ፡- ማለት በኢንስቲትዩቱ በቋሚነት ወይም እንደአስፈላጊነቱ በኮንትራት ውል ስምምነት የተቀጠረ ሠራተኛ ነው፡፡

2.9 ቤተሰብ፡- ማለት ሠራተኛው፣ የሠራተኛው ባል/ሚስት፣ ልጅ፣ ጉዲፈቻ ልጅ እና በቤተሰብ ሕጉ መሠረት በእነርሱ ስር የሚተዳደሩ የቅርብ ዘመዶች ናቸው፡፡

2.10 የቤተሰብ ብዛት፡- ማለት የሠራተኛው የትዳር አጋር፣ ልጅ፣ የጉዲፈቻ ልጅ ወይም በቤተሰብ ሕጉ መሠረት በስራቸው የሚተዳደሩ ሰዎች ብዛት ነው፡፡

2.11 የማዕከል የመኖሪያ ቤት ድልድል ኮሚቴ፡- ማለት የማዕከል የመኖሪያ ቤት ድልድል /ሽግሽግ የሚሠራና የመኖሪያ ቤት አጠቃቀምን በተመለከተ የማዕከሉን ዳይሬክተር የሚያማክር ኮሚቴ ነው፡፡

2.12 የረዥም ጊዜ ስልጠና፡- ማለት የትምህርት ደረጃ ለውጥ የሚያስገኝ ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ስልጠና ማለት ነው፡፡

2.13 የአጭር ጊዜ ሥልጠና፡- ማለት የትምህርት ደረጃ ለውጥ የማያስገኝ እስከ አንድ ዓመት ለሚቆይ ጊዜ የሚሰጥ ስልጠና ነው፡፡

2.14 የጋራ የቤት የመገልገያ ዕቃዎች፡- ማለት በጋራ ቤት የተከራዩ ወይም በሥራ አስፈላጊነት በነጻ እንዲኖሩበት የተፈቀደላቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሠራተኞች በጋራ የሚገለገሉባቸው የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ናቸው፡፡

2.15 የአገልግሎት ዘመን፡- ማለት በኢንስቲትዩቱ ወይም በሌላ የምርምር ተቋም ወይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በተመራማሪነት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ከተቀጠረበት ጊዜ እስከ ቤት ድልድሉ ጊዜ ድረስ የሚቆጠር የአገልግሎት ዘመን ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ቤቶችና የመገልገያ ዕቃዎች ተጠቃሚ ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ምርምሩ በሚካሄድበት አካባቢ በቅርበት በመኖር የምርምሩን ሥራ በተረጋጋ ሁኔታ እንዲያከናውኑ የመኖሪያ ቤት በተገነባላቸው ማዕከላት የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ማቅረብ አስፈልጓል፤

4.1 ተመራማሪው ከመደበኛ የሥራ ሰዓት በተጨማሪ በቢሮ፣ በላቦራቶሪና በመሳሰሉት ቦታዎች በቅርብ በመገኘት የምርምር ሥራውን ለማከናወን፤

4.2 ተመራማሪዎች አንድ ቦታ በመኖራቸው ያላቸውን እውቀትና ልምድ እርስ በእርስ ለመለዋወጥ የተሻለ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር፤

4.3 በአንዳንድ የምርምር ማዕከላት አካባቢ ካለው ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ተመራማሪዎችን ሊያኖር የሚያስችል የተሟላ የኪራይ ቤት በቅርበት ባለመኖሩ፣ ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት ለማቅረብ፤

4.4 በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በቅርበት እንዲገኙ የሚፈለጉ ሠራተኞች ከመደበኛ የሥራ ሰዓታቸው ውጭ ለሚሰሩ ሥራዎች ሙያዊ ድጋፍ መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ፤

4.5 ከሥራቸው ባህሪ የተነሳ በቅርብ በመገኘት ለምርምር ድጋፍ ሰጭ የሆኑ ሠራተኞችን ለማበረታታትና ለማትጋት ነው፡፡

## 5. የመኖሪያ ቤት ድልድል መመዘኛ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | የመመዘኛ መስፈርት | መቶኛ (100%) |
|---|---|---|
| ሀ | ለተመራማሪዎች | |
| 1 | የሥራ ደረጃ | 50 |
| 2 | የሥራ ኃላፊነት | 20 |
| 3 | የቤተሰብ ብዛት | 15 |
| 4 | የአገልግሎት ዘመን | 15 |
| ለ | ለአስተዳደር ዘርፍ ባለሙያ | |
| 1 | የሥራ ደረጃ | 50 |
| 2 | የአገልግሎት ዘመን | 25 |
| 3 | የቤተሰብ ብዛት | 25 |

## 6. የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ አፈጻጸም ቅደም ተከተል

6.1 የሠራተኛው የሥራ ባህሪ ወይም በማዕከል የመኖር አስፈላጊነት ሲኖር ያለውድድር ቅድሚያ ያሰጣል፤

6.2 በውድድር የነጥብ ብልጫ የሚሰጥ፤

6.3 አገልግሎት ከሚሰጡ የማዕከሉ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ 70% ለተመራማሪ እና ለቴክኒክ ሰራተኞች፤ እንዲሁም ቀሪው 30% ለአስተዳደር ዘርፍ ሠራተኞች ሆኖ አፈፃፀሙን በተመለከተ በውጤታቸው ቅደም ተከተል መሰረት ይደለደላል፡፡

## 7. በሥራ ባህሪ ምክንያት መኖሪያ ቤት ያለ ውድድር የሚፈቀድላቸው ሠራተኞች

7.1 ከላይ በአንቀጽ 6.1 በተቀመጠው መሰረት በማዕከል ካሉት የተሻለ ደረጃ ካላቸው መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ያለ ውድድር የተፈቀደላቸው፤

7.1.1 የማዕከል ዳይሬክተር፣

7.1.2 መሪ ተመራማሪ (ከአንድ በላይ ሆነው ካመለከቱ የቤተሰብ ሁኔታቸው ከግምት ውስጥ በማስገባት እርስ በርሳቸው የሚወዳደሩ ይሆናል)፣

7.1.3 ተቋሙ በልዩ ሁኔታ በማዕከሉ የሚመድባቸው የምርምር ፕሮጀክት የውጭ አገር ኤክስፐርቶች፣

7.1.4 በልዩ ስምምነት ለተቀጠሩ ከፍተኛ ባለሙያዎች፣

7.1.5 የብቃትና ሰው ሀብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ፣

7.1.6 የፋይናንስና ግዥ ሥራ አስፈጻሚ፣

7.1.7 የመሰረታዊ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ ናቸው፡፡

7.2 ቀደም ሲል የነበረበትን የመኖሪያ ቤት በሌላ ኃላፊነት ምክንያት ያስረከበ ተመራማሪ ተመልሶ ማዕከሉ ላይ ሲመደብ ያለውድድር የመኖሪያ ቤት እንዲያገኝ ይደረጋል፤

7.3 በአካል ጉዳት ምክንያት ከሩቅ ተመላልሶ ለመሥራት የማይችል ተመራማሪ/ ባለሙያ እንደማዕከሉ ተጨባጭ ሁኔታ ደረጃው በሚመጥነው የመኖሪያ ቤት ያለውድድር ይሰጠዋል፡፡

8. በማዕከሉ ውስጥ ባሉ ደረጃ 3 እና በታች ቤቶች ውስጥ ያለ ውድድር እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው

8.1 አንድ የእንስሳት ጤና ባለሙያ፣

8.2 አንድ ኤሌክትሪሺያን፣

8.3 አንድ ሾፌር፣

8.4 የቴክኖሎጂ ብዜት አስተባባሪ፣

8.5 የሚቲሮዎሎጂካል ፎርካስትንግ ቴክኒሽያን፣

8.6 የውኃ ፓምፕ ኦፕሬተር (ከፍተኛ የመስኖ ግንባታና ጎርፍ አደጋ ባለባቸው ማዕከላት) ናቸው፡፡

9. የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ መመዘኛ መስፈርቶችና የመወዳደሪያ ነጥብ አሰጣጥ

ሠንጠረዥ 1፡ ለተመራማሪዎች የሥራ ደረጃና የኃላፊነት ቦታዎች የሚሰጥ ነጥብ

| አጠቃላይ የማወዳደሪያ መስፈርቶች | የሚሰጥ ነጥብ |
|---|---|
| ሀ/ የተመራማሪነት ደረጃ | 50% |
| መሪ ተመራማሪ | 50 |
| ከፍተኛ ተመራማሪ | 45 |
| ተመራማሪ II | 42 |

| | |
|---|---|
| ተመራማሪ I | 40 |
| ተባባሪ ተመራማሪ | 37 |
| ረዳት ተመራማሪ II | 32 |
| ረዳት ተመራማሪ I | 25 |
| ጀማሪ ተመራማሪ | 20 |
| ለ/ ለኃላፊነት ቦታ የሚሰጥ ነጥብ | 20% |
| የፕሮግራም አስተባባሪ | 20 |
| የማዕከል የዘርፍ ኃላፊ | 15 |
| የፕሮጀክት አስተባባሪ | 10 |
| ሐ/ ለአገልግሎት ዘመን የሚሰጥ ነጥብ | 15% |
| ከ15 ዓመት በላይ | 15 |
| ከ10 ዓመት እስከ 14 ዓመት | 12 |
| ከ6 ዓመት እስከ 9 ዓመት | 9 |
| እስከ 5 ዓመት | 5 |
| መ/ ለቤተሰብ ብዛት የሚሰጥ ነጥብ | 15% |
| ባለትዳር እና ከ 3 በላይ የቤተሰብ አባላት | 15 |
| ባለትዳር እና ከ 1 እስከ 2 የቤተሰብ አባላት | 12 |
| ባለትዳር | 9 |
| ያላገባ | 5 |

ሠንጠረዥ 2፡ ለአስተዳደር ዘርፍ ሠራተኞች የሥራ ደረጃና የኃላፊነት ቦታዎች የሚሰጥ ነጥብ

| አጠቃላይ የማወዳደሪያ መስፈርቶች | የሚሰጥ ነጥብ |
|---|---|
| ሀ/ ለአስተዳደር ዘርፍ ባለሙያዎች | 50% |
| ቡድን መሪ፣ የጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ | 50 |
| ባለሙያ IV | 45 |
| ባለሙያ III | 40 |
| ባለሙያ II | 35 |
| ባለሙያ I | 30 |
| ሠራተኛ | 25 |
| ለ/ ለአገልግሎት ዘመን የሚሰጥ ነጥብ | 15% |
| ከ15 ዓመት በላይ | 15 |
| ከ10 ዓመት እስከ 14 ዓመት | 12 |

| | |
|---|---|
| ከ6 ዓመት እስከ 9 ዓመት | 9 |
| እስከ 5 ዓመት | 5 |
| ሐ/ ለቤተሰብ ብዛት የሚሰጥ ነጥብ | 15% |
| ባለትዳር እና ከ 3 በላይ የቤተሰብ አባላት | 15 |
| ባለትዳር እና ከ 1 እስከ 2 የቤተሰብ አባላት | 12 |
| ባለትዳር | 8 |
| ያላገባ | 5 |

## 10. የመኖሪያ ቤትና መገልገያ ዕቃዎች ድልድል/ሽግሽግ አስፈጻሚ አካላት

10.1 የማዕከላት ዳይሬክተሮች ለመመሪያው ተፈጻሚነት አግባብነት ያለው ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

10.2 የማዕከል የመሰረታዊ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ የመኖሪያ ቤቱን ለተመደበለት ሰው ያስረክባል፣ ተመላሽ ሲሆን ይረከባል፣ የጥገና አገልግሎት ይሰጣል እንዲሁም የመብራትና ውኃ ፍጆታዎች ወቅቱን ጠብቆ በነዋሪዎች መከፈላቸውን ይከታተላል፡፡

10.3 የማዕከል ዳይሬክተር በማዕከሉን የመኖሪያ ቤት ድልድል ኮሚቴ ይሰይማል የሚሰየመው ኮሚቴ ቢያንስ አንድ ሴት ሠራተኛን አባል ማድረግ ይኖርበታል፤ ኮሚቴ ሰርቶ የሚያቀርባቸውን ውሳኔ ሀሳቦች መርምሮ ያጸድቃል፡፡

## 11. የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

11.1 የመኖሪያ ቤት ድልድል/ሽግሽግ ኮሚቴ የመኖሪያ ቤት ባለባቸው ማዕከላት ይቋቋማል፡፡

11.2 የኮሚቴው ተጠሪነት ለማዕከሉ ዳይሬክተር ይሆናል፡፡

11.3 የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ነው፡፡

11.4 በዚህ መመሪያ መሠረት የመኖሪያ ቤት ድልድልና ሽግሽግ በማድረግ ውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

11.5 የመኖሪያ ቤትና የመገልገያ ዕቃዎችን አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የቤቶቹን አጠቃላይ ይዘት በማየት የማስተካከያ ሃሳብ ለማዕከል ዳይሬክተር ያቀርባል፡፡

## 12. የመኖሪያ ቤት ድልድል ኮሚቴ አባላት

12.1 የመሰረታዊ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ . . . . ………. ሰብሳቢ

12.2 የብቃትና ሰው ኃብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ . . . . . ፀሐፊ

12.3 በተመራማሪዎች የሚመረጥ 2 ተመራማሪዎች …………… አባል

12.4 በማዕከል ዳይሬክተር የሚትመደብ ተወካይ ………. አባል ይሆናሉ፡፡

## 13. የመኖሪያ ቤትና የቤት መገልገያ ዕቃዎች ድልድል/ሽግሽግ አፈጻጸም፣ አያያዝ እና አጠቃቀም

13.1 ውድድሩ የሚከናወነው ተመራማሪው ከተመራማሪ እንዲሁም የአስተዳደር ዘርፍ ከአስተዳደር ዘርፍ ጋር ነው፡፡ እንደምርምር ማዕከሉ ተጨባጭ ሁኔታ ያሉትን ቤቶች ለተመራማሪዎችና ለአስተዳደር ዘርፍ ባለሙያዎች የመለየት ሥራ የማዕከሉ ማኔጅመንት ይሆናል፡፡

13.2 ለውድድር የቀረቡ ሠራተኞች ነጥብ ድምር እኩል ከሆነ ለሴት ተወዳዳሪ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

13.3 ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይ ፆታ ከሆኑ በመጀመሪያ ከፍተኛ የሥራ ደረጃ ያለው፤ ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ከሆኑ በቤተሰብ ብዛት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

13.4 ከላይ በተቀመጡት መንገዶች መለየት ካልተቻለና ለውድድር የቀረቡ ሠራተኞች ነጥብ ድምር እኩል ከሆነ የመኖሪያ ቤት ድልድል ተወዳዳሪዎች ወይም ተወካይ በተገኙበት በሚወጣ ዕጣ ይሆናል፤

13.5 ኢንስቲትዩቱ ለሠራተኞቹ የመኖሪያ ቤትና የቤት መገልገያ ዕቃዎችን እንደአስፈላጊነቱ የሚያቀርብ ቢሆንም ይህንን ማሟላት ግን እንደ ግዴታ ሊወሰድ አይገባም፤

13.6 ከማዕከል ወደ ማዕከል በሚደረግ ዝውውር በማዕከሉ ቤት ሊያገኙ የሚችሉት በመመሪያው መሠረት ይሆናል፡፡

13.7 ባለትዳሮችና የቤተሰብ ኃላፊዎች ስለቤተሰባቸው ህጋዊ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ከቤተሰብ ጋር መኖር የሚቻለው ለቤተሰብ በተፈቀደ መኖሪያ ቤቶች ብቻ ነው፡፡

13.8 ሠራተኛው አብረውት የሚኖሩት ቤተሰቦችና እንግዶች ለሚፈጥሩት ችግር ተጠያቂ ነው፡፡

13.9 የቤቱ ተጠቃሚ አጠቃላይ የመኖሪያ ቤቱንና የአካባቢውን ውበትና ፅዳት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

13.10 ማዕከሉ መኖሪያ ቤቱን አሳማኝ ለሆነ ሥራ ከፈለገው የሦስት ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ሠራተኛው የተረከበውን ቤት ያስረክባል፡፡ ሆኖም ግን ሠራተኛው በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት በድጋሚ መወዳደር ሳያስፈልገው ተመሳሳይ ቤት በቅድሚያ ያገኛል፡፡

13.11 ሠራተኛው የተረከበውን መኖሪያ ቤትና የመኖሪያ ቤት መገልገያ ዕቃዎች እንዲያስረክብ በተጠየቀበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስረከበ ቤቱ በኮሚቴ ታሽጎ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

13.12 በመኖሪያ ቤቱ ላይ ከነዋሪው አቅም ወይም ቁጥጥር በላይ ለሆኑ የንብረት ጉዳቶችና ብልሽቶች ኢንስቲትዩቱ/ማዕከሉ ተገቢውን ጥገና ያደርጋል፡፡

13.13 ለሾፌር የሚሰጥ ቤትን በተመለከተ ሥራው በዙር ተራ የሚከናወን ስለሆነ የቤተሰብ መኖሪያ ቤት ያልሆነ ለማደሪያነት ብቻ የሚያገለግል አንድ ክፍል ቤት ይሰጠዋል፡፡

13.14 የመኖሪያ ቤት ዕድሳትን በተመለከተ ማዕከሉ በየአምስት ዓመቱ ኢንስቲትዩቱን በማሳወቅ የሚታደስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

13.15 አነስተኛ ጥገናዎችን በተመለከተ ማዕከላት በጀት በማስያዝ የሚፈልጉትን ዕቃዎች አሟልተው ጥገናው እንዲከናወን ያደርጋሉ፡፡

13.16 ለባለትዳር ሠራተኞች በማወዳደሪያ መስፈርቱ መሰረት አብላጫ ነጥብ ለውድድር ይያዝለታል፡፡

13.17 በውድድር ጊዜ ከስድስት ወራት በላይ ያለ አገልግሎት ወደ ሚቀጥለው ዓመት ይታሰብለታል፡፡

13.18 የተሰጠውን የመኖሪያ ቤት ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት አይችልም፡፡

13.19 የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ የተጠቀመበትን መኖሪያ ቤት የመብራት፣ የውኃ፣ የስልክ፣ የኢንተርኔት፣ የጽዳትና መሰል ፍጆታዎችን ወቅቱን ጠብቆ የመክፍል ግዴታ አለበት፡፡

13.20 የተሰጠውን የመኖሪያ ቤት ከሦስት ወራት በላይ ሳይጠቀምበት ዘግቶ ማስቀመጥ አይችልም፤ ይህ ከተደረገ መኖሪያ ቤቱን በገዛ ፈቃዱ እንደስረከበ ይቆጠራል፡፡

13.21 የተሰጠውን መኖሪያ ቤት በማዕከል ዳይሬክተር በጽሁፍ ካልተፈቀደለት በስተቀር ቀይሮ ሌላ ቤት ውስጥ መግባት አይችልም፡፡

## 14. የመኖሪያ ቤትና የቤት መገልገያ ዕቃዎችን በተመለከተ የነዋሪዎች ግዴታ

14.1 መኖሪያ ቤትን መገልገል የሚቻለው ለመኖሪያ ቤት በተዘጋጀው ውልና የመረካከቢያ ሰነድ ላይ ተገልጋዩ ፈርሞ ሲቀበል ብቻ ነው፡፡

14.2 በማናቸውም ምክንያት ያለበትን ማዕከል የሚለቅ ሠራተኛ የመኖሪያ ቤትና የቤት ዕቃዎች የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

14.3 ማንኛውም የኢንስቲትዩቱ ሠራተኛ እንዲኖርበት የተፈቀደለትን መኖሪያ ቤት ከሌላ ሠራተኛ ጋር በራሱ ፈቃድ መለዋወጥ፣ መከፋፈል፣ ማፍረስ፣ ከባድ እድሳትም ሆነ ጥገና ማድረግ እንዲሁም ከመኖሪያነት ውጭ ለሌላ አገልግሎት ማዋል አይፈቀድም፡፡

14.4 ማንኛውም ሠራተኛ ከማዕከሉ እውቅና ውጭ የተሰጠውን መኖሪያ ቤት ያለበቂ ማስረጃ ከሦስት ወር በላይ ቆልፎ ከተገኘ መ/ቤቱ በኮሚቴ ቤቱን ተረክቦ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

14.5 በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ለረጅም ጊዜ ሥልጠና የሚሄድ ሠራተኛ በኪራይም ሆነ በነጻ እንዲኖርበት የተረከበውን የመኖሪያ ቤትና ንብረት ከመሄዱ በፊት የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

14.6 ማንኛውም የኢንስቲትዩት ባልደረባ ለሚኖርበት ቤትና ለግቢው እንዲሁም ለተረከበው ንብረት ተገቢውን ጥንቃቄና እንክብካቤ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ የመኖሪያ ቤት እና የመገልገያ ዕቃ ብልሽት ከጥንቃቄ ጉድለት ሆኖ ሲገኝ በሚመለከተው ባለሙያ ተረጋግጦ በማዕከሉ በኩል የጥገና አገልግሎት የሚደረግ ይሆናል፤ ወጭውን ተገልጋዩ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

14.7 አገልግሎት የሚሰጡም ሆነ የማይሰጡ የመኖሪያ ቤት መገልገያ ዕቃዎች የንብረት ማዛዋወሪያ ቅፅ ሳይሞላ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላ ቤት ማዛወር አይቻልም፡፡

14.8 ማንኛውም የኢንስቲትዩት ባልደረባ በመኖሪያ ቤት ውስጥ የማያገለግሉ ንብረቶች በሚኖሩበት ወቅት የማስወገጃ ፎርም ሞልቶ ወደ መሰረታዊ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ እንዲመለሱ ማድረግ አለበት፡፡

14.9 በራሱ ፈቃድና በጡረታ መሰሪያ ቤቱን የሚለቅ ሠራተኛ ከአንድ ወር በፊት ቤቱንና የተረከባቸውን ንብረቶች ማስረከብ አለበት፡፡

14.10 ከመስሪያ ቤቱ በሞት የተለየ ባልደረባ ቤተሰቦቹ እንዳይጉላሉ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ጊዜ ተሰጥቶ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ቤቱና ንብረቱን ቤተሰቦቹ ያስረክባሉ፡፡

14.11 በከባድ ህመም ወይም በደረሰ አደጋ ምክንያት ከምድብ የሥራ ቦታው ላይ የተለየ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ሠራተኛ በህግ የተፈቀደለትን ፈቃዶች ካጠናቀቀ በኋላ ቤተሰቦቹ እንዳይጉላሉ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲቆይ ተደርጐ ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ የተረከበውን ቤትና ንብረት ያስረክባል፡፡

14.12 ሠራተኛው በሥራ ላይ እያለ በተፈጠረ ጥፋት ምክንያት በወንጀል ተጠርጥሮ በህግ ቁጥጥር ስር በሚሆንበት ወቅት በቁጥጥር ስር ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ቤተሰቦቹ እንዳይጉላሉ ለተጨማሪ ለአንድ ዓመት እንዲቆይ ተደርጐ ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ የተረከበውን ቤትና ንብረት ቤተሰቦቹ ያስረክባሉ፡፡

14.13 የመኖሪያ ቤት መገልገያ ቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ በየዓመቱ ሲካሄድ ሠራተኛው የተረከበውን ንብረት የማስቆጠር ግዴታ አለበት፡፡

14.14 ሠራተኛው በሚኖርበት መኖሪያ ቤትና በሚገለገልባቸው የመኖሪያ ቤት መገልገያ ዕቃዎች ላይ ጥፋት ወይም ብልሽት ቢደርስ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ጥፋቱ የተከሰተው ከጥንቃቄ ጉድለትና አያያዝ ከሆነ ሠራተኛው ለጥፍቱ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

14.15 በመኖሪያ ቤት ጊቢ ውስጥ የቤት እንስሳት ማርባትና ንብ ማነብ አይቻልም፡፡ እንዲሁም ባልተፈቀዱ ቦታዎችም እርድ መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

14.16 ይህን የመኖሪያ ቤት መመሪያ የማያከብርና ድንጋጌዎችን ጥሶ የተገኘ ሠራተኛ ድርጊቱን ለመፈጸሙ በማዕከሉ ሲረጋገጥ በመጀመሪያ በጽሁፍ የሚሰጥ የቃል ማስጠንቀቂያ፣ ቀጥሎ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የማይታረም ከሆነ የማዕከሉ ዳይሬክተር ቤቱን እንዲለቅ ያደርጋል፡፡

14.17 ለመኖሪያ ቤት ድልድል የሚያመለክት ሠራተኛ ባለትዳርነቱን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ የጋብቻ ሰርተፊኬት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

14.18 ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመስማማት የተረከባቸው መኖሪያ ቤቶች የኪራይ ተመን አከራይ በሚጠይቀው ተመን መሰረት ነዋሪው ክፍያ ይፈፃማል፡፡

## 15. የመኖሪያ ቤት አጠያየቅና አሰጣጥ ሂደት

15.1 በማዕከሉ ውስጥ ያሉትን ክፍት መኖሪያ ቤቶች ግልጽ የሆነ መታወቂያ ቁጥር በመስጠት ለቤት ፈላጊዎች የምዝገባ ጥሪ በብቃትና ሰው ኃብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ ይገለጻል፡፡

15.2 በተቋሙ የመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ያለውድድርም ይሁን በውድድር እንዲኖሩ የተወሰነላቸው ሠራተኞች ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአስር ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡

15.3 የመኖሪያ ቤት ድልድል ኮሚቴው የአመልካቾችን ዝርዝር እና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱትን አስፈላጊ መረጃዎች በማጠናቀር በግልጽነት እንዲወዳደሩ ማድረግ አለበት፡፡

15.4 ኮሚቴው በማስታወቂያ በወጡት የመኖሪያ ቤቶች ላይ የተመዘገቡና በመመሪያው መሠረት የሚገባቸውን ተወዳዳሪዎች ዝርዝር በግልጽ በማዕከሉ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት እንዲገለጽ ማድረግ አለበት፡፡

15.5 ከላይ በቁጥር 15.4 ላይ የተገለፀው ውጤት በማስታወቂያ ሰሌዳ በተገለፀ የቤት ድልድል ውጤት ላይ ቅሬታ ካለው ለማዕከሉ በጽሑፍ ውጤቱ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

15.6 ማዕከሉ የቀረበውን ቅሬታ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ መርምሮ ለቅሬታ አቅራቢው ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

15.7 የማዕከሉ የመኖሪያ ቤት ድልድል ኮሚቴ በቀረበው ቅሬታ ላይ ከማዕከሉ የተሰጠውን ምላሽ በማካተት የድልድል ቃለ ጉባዔ አዘጋጅቶ በማዕከሉ ዳይሬክተር ያጸድቃል፡፡

15.8 በውሳኔው መሠረት ቤቱ የተመደበለት/ላቸው ሠራተኛ/ኞች በዚህ መመሪያ ውስጥ በአባሪነት … በተካተተው ቅጽ አማካይነት የቤት ርክክብ ውል ይፈራረማል፡፡

15.9 የውል ስምምነቱን መሠረት ባደረገ መልኩ ለሠራተኛው የተመደበውን የመኖሪያ ቤት እንዲረከብ በሚመለከተው ኃላፊ ደብዳቤ ይሰጠዋል፡፡

## 16. የመኖሪያ ቤት ኪራይ ተመን

ሠንጠረዥ 3፡ የሆለታ፣ የብሔራዊ ግብርና ባዮቴክኖሎጂ፣ የደብረ ዘይት፣ ብሔራዊ ዓሳ፣ አምቦ፣ ቁሉምሳ እና ፎገራ ብሔራዊ የሩዝ ምርምር ማዕከላት የመኖሪያ ቤት ተመን በቤት ደረጃ

| የቤት ደረጃ | የኪራይ መጠን (ብር) |
|---|---|
| ደረጃ 1 | 3000.00 |
| ደረጃ 2 | 2500.00 |
| ደረጃ 3 | 1500.00 |
| ደረጃ 4 | 800.00 |
| ደረጃ 5 | 300.00 |

ሠንጠረዥ 4፡ ወንዶገነት፣ ጭሮ፣ አሶሳ፣ ፓዊ፣ ቴፒ፣ መሆኒ፣ ወረር ግብርና ምርምር ማዕከላት ተመን በቤት ደረጃ

| የቤት ደረጃ | የኪራይ መጠን (ብር) |
|---|---|
| ደረጃ 1 | 2000.00 |
| ደረጃ 2 | 1500.00 |
| ደረጃ 3 | 1000.00 |
| ደረጃ 4 | 500.00 |
| ደረጃ 5 | 200.00 |

ሠንጠረዥ 5፡ የጊራ፣ ሐሩ፣ አዋዳ፣ አድአ በርጋ መለስተኛ ግብርና ምርምር ማዕከላት ተመን በቤት ደረጃ

| የቤት ደረጃ | የኪራይ መጠን (ብር) |
|---|---|
| ደረጃ 1 | 700.00 |
| ደረጃ 2 | 400.00 |
| ደረጃ 3 | 250.00 |
| ደረጃ 4 | 150.00 |
| ደረጃ 5 | 100.00 |

16. **የመመሪያው ተፈጻሚነት**

ይህ መመሪያ የሠራተኛ መኖሪያ ቤት በተገነባባቸውና ከመንግሥት ተረክቦ በሚያስተዳድራቸው በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ስር በሚተዳደሩ ማናቸውም የምርምር ማዕከላትና መለስተኛ ማዕከላት ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

17. **መመሪያውን ስለማሻሻል** መመሪያው እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ጊዜው ሁኔታ ሊሻሻል ይችላል፡፡

18. **የተሻሩ መመሪያዎች**

ቀደም ሲል ከነሐሴ 2004 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የነበረው "የመኖሪያ ቤትና መገልገያ ዕቃዎች ድልድልና አጠጠቃቀም መመሪያ" በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

19. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ከጸደቀበት ከቀን ----------------- ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

---------------

ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

አባሪ

1፡

በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት  የ
ምርምር ማዕከል
የመኖሪያ ቤት ውስጥ እንዲኖሩ የተመዘገቡ የቤተሰቦች ዝርዝር

የሠራተ□ው ስም ____________________

እንዲኖርበት የተሰጠው የመኖሪያ ቤት መለያ ቁጥር _________________________

የመኖሪያ ቤቱን የተረከበበት ቀን__________________

በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እንዲያኖራቸው ያስመዘገባቸው ቤተሰቦች ዝርዝር (ከአንድ ወር በላይ በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች መመዝገብ ይኖርባቸዋል)፡

| ተ.ቁ. | የቤተሰብ ስም | ዝምድና | በቤቱ ውስጥ እንዲኖሩ የተፈቀደበት ጊዜ (ከ እስከ ________________.) | የነዋሪው ፊርማ | የሥራው ኃላፊ ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |